ጥር 2017 ዕትም

# የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# ዜና መጽሔት



**ጥር 5:2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) የነዳጅ ዋጋ ማሻሻያን በሚመለከት መግለጫ ሰተዋል። የነዳጅ ዋጋ ዋናው ማነጻጸሪያ የዓለም ዋጋ ነው ያሉት ሚኒስትሩ የዓለም የነዳጅ ዋጋ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማንም ሰው በቀላሉ መረጃ ማግኘት ይችላል ብለዋል።

ዝቅተኛ የኑሮ ድረጃ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳይጎዱ መንግስት ከፍተኛ ጫና ተሸክሞ በርካታ ቢሊዮን ብር በመመደብ ነዳጅን በመደጎም ላይ ይገኛል። በአሁኑም የዋጋ ማስተካከያ ከዓለም ዋጋ አንፃር ምንም ትርፍ ሳይያዝበት መተላለፍ ከነበረበት ዋጋ መንግስት በአሁን ወቅት በቤንዚን 21 ብር በናፍጣ ደግሞ 28 ብር ድጎማ በማድረግ ጫናውን የተሸከመ መሆኑን ህብረተሰባችን እንዲረዳ እንፈልጋለን ብለዋል ክቡር ሚኒስትሩ።

በዚህ መልኩ በገባ የነዳጅ ምርት ላይ በኮንትሮባንድ፣ በአቅርቦትና በክምችት ረገድ ችግሮች ይስተዋላሉ። ከውጪ ንግድ የሚናገኘውን ገቢ መስዋዕት የምናደርግበትን ይህ ስትራተጂክ ግብይት ሲባክን መንግስት ችላ የሚለው ጉዳይ እንደማይሆንም አስምረውበታል። የአቅርቦት እጥረት ሳይኖር ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት እንዲፈጠር ካደረጉ መካከል 250 የሚጠጉ ቦቴዎች ከ10 እስከ 15 ቀናት ጫካ እና ዱር ውስጥ ቆመው ከፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀትና በተክኖሎጂ በመታገዝ መያዝ መቻሉን ተናግረዋል። ህገወት ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ ኩባንያዎች ለ6 ወራት ከነዳጅ ግብይት እንዲወጡና ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ እንዲቀጡ ተገርጓል። መሰል እርምጃዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡

**ጥር 7 ፡ 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በአዘርባጃን ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ያልቼን ራፊየቭ የተመራን ልዑክ ተቀብለው የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነትን ማጠናከር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ገንቢ ውይይት አድርገዋል። ውይይታቸው በሀገራቱ መካከል ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ለማጎልበት ትልቅ ምዕራፍ የሚከፍትና እምቅ ዕድሎችን ለመለየት ያስቻለን መሆኑን ሚኒስትሩ ተናግረዋል።





**ጥር 9 ፡ 2017** ክቡር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በቻይና መንግስት ምክር ቤት የልማት ምርምር ማዕከል ፕሬዝዳንት ሉ ሃኦ የተመራውን ልዑክ ተቀብለው በኢትዮጵያና ቻይና የንግድ ግንኙነት ዙሪያ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል። በሁለቱ ሃገራት መካከል ጠንካራ የንግድ ግንኙነት ያለ ቢሆንም ወደፊት የላቀ ትብብር ማድረግ የሚቻልባቸውን መስኮች ተለይተው የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረሳቸውን ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

በተለይ ኢትዮጵያ ወደ ቻይና የምትልካቸውን ምርቶች ማሳደግና የሁለቱን ሃገራት ኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተጨማሪ መስኮችን የዳሰሰ ውጤታማ ውይይት አድርገዋል። የልዑካን ቡድኑ አባላት የጥራት መንድርን የጎበኙ ሲሆን ኢትዮጵያ ለጥራት ያላትን ቁርጠኝነት በሚገባ ለማሳየት ተችሏል ብለዋል።





**ጥር 12 : 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) “በጥራት ወደ ተሳለጠ የንግድ ስርዓት” በሚል መሪ ቃል የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የስራ አፈጻጸምን ገምግመዋል።

የስራ አፈጻጸም ግምገማው ላይ ባለፉት ስድስት ወራት የአሰራር ማሻሻዎችን በማድረግ ያገኘናቸው አመርቂ ውጤቶችን ለቀጣይ የላቀ ኃላፊነት በሚያዘጋጀን አግባብ የሚታይ መሆኑን ክቡር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

በግምገማ መድረኩ ከተጠቀሱ ስኬቶች መካከል፡ ባለፉት ስድስት ወራት በወጪ ንግድ ዘርፍ ወደ 3.28 ቢሊየን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በግምገማው ላይ ሌላው የተጠቀሰው ስኬት የጥራት መንደር ኢትዮጵያን በሚወክልና በሚያስደንቅ ደረጃ ለሃገር ኩራት ማዕከል ሆኖ መጠናቀቁ ነው።

በኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ ለንግድ ስርዓት ምቹ እንዲሆን ውጤታማ ስራ መሰራቱም ተገልጻል። በዚህ ረገድ ብልሹ አሰራሮችን ከማረም አንጻር ህገ ወጥ ተግባር በፈጸሙ የተቋሙ ሰራተኞች ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል። በበጀት ዓመቱ ባለፉት ስድስት ወራት ከ2 ሚሊዮን 50 ሺህ በላይ የንግድና ምዘገባ ፍቃድ አገልግሎት ተሰቷል። ይህ ውጤት ያለፈው በጀት ዓመት ከተከናወነው 2.4 ሚሊዮን ዓመታዊ አፈጻጸም አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ አፈፃፀም ሆኖ ተመዝግቧል።

ነዳጅ ግብይትን ሰርዓት ለማስያዝ በተሰራ ስራ በህገ-ወጥ መንገድ ሲጓጓዝ የነበረ 325 ሺ ሊትር ነዳጅ በቁጥጥር ስር ውሏል። ኩባንያዎች 116 ሚሊዮን ብር እንዲቀጡ ተደርጓል። የሲሚንቶ ግብይት ላይ በተወሰደ የአሰራር ሰርዓት ማሻሻያ የተረጋጋ አቅርቦትና ግብይት እንዲኖር በመደረጉ ዋጋው በግማሽ ቀንሷል። በተመሳሳይ መንገድ የጨው ግበይት ሪፎርም በማድረጋችን በጥቂት ናጋዴዎች በሞኖፖሊ ተይዞ የነበረውን ግብይት በፍትሃዊነት ለሁሉም ክፍት እንዲሆን ተደርጓል።

የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት ተቋርጦ ከነበረበት ምዕራፍ በማውጣት ወደ ንቁ ድርድር አውድ የገባን ሲሆን ለቀጣይ 5ኛ ዙር ድርድርም ብቃት ያላቸው ሙያተኞችን በማደራጀት በቂ ዝግጅት በመድረግ ላይ ይገኛል።



**ጥር 13 ፡ 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በኢትዮ-ሎጅስቲክስ የዘርፍ ማኅበራት በተዘጋጀው የቢዝነስ ማኅልበቻ ኮንፈረንስ ላይ ተገኝተው ከጂቡቲ ጋር ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት አስፈላጊነት እና የኢትዮጵያ መንግስት በቀጣናው የንግድ እድሎችን ለማሳደግ ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል፡፡

ከጂቡቲ ጋር ያለን የጸና ትብብርና የመሠረተ ልማት ትስስር ለጋራ ዕድገትና ለአዳዲስ ዕድሎች ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ተግዳሮቶችን በማስወገድ ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ስምምነት ጋር የሚስማማና አስተማማኝ የትብብር ማዕቀፍን እውን ለማድረግ በትጋት እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡ ፡ ማኑፋክቸሪንግና ግብርናን መሰረት ያደረገና ብዝሃነት ያለውን የውጭ ንግድ ለማስፋት እየሰራን ላለነው ስራ ጂቡቲ ስትራቴጂክ አጋራችን ናት ብለዋል፡፡



በተመሳሳይ ዕለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽንን የመጋዘን አገልግሎት ተዘዋውረን ጎብተዋል፡፡ ተቋሙ በመንግስት የተሰጠውን መሰረታዊ የምግብ ፍጆታ፣ ልዩ ልዩ ምርትና ሸቀጥ የማቅረብና የማሰራጨት ተልዕኮውን በብቃት እንዲወጣ የሚያስችሉ የአሰራር ሪፎርሞች እንዲተገበር አቅጣጫ አስቀምጠዋል፡፡ የኮርፖሬሽኑ አመራሮችም የተሰጣቸውን ተልዕኮ በላቀ ውጤትና የስራ ጥራት እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡ የሪፎርም ስራዎቹ የትግበራ ሂደትና ውጤታቸውን በቀጣይነት እንደሚገመግሙም ተናግረዋል፡፡





**ጥር 14 : 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በጃፓን የንግድና ኢንቨስትመንት ሲምፖዚየም ላይ ተገኝተው መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉት አንዱ መሆኑን ያወሱት ሚኒስትሩ በንግድ እና ኢንቨስትመንት ረገድም በርካታ እድሎችን ማቅረቡን በመድረኩ ላይ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በወጪ ንግድ ከፍተኛ እድገት በማስመዝገብ በኢኮኖሚ ጉዞዋ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ትገኛለችም ብለዋል፡፡ ለአብነትም በበጀት ዓመቱ ባለፉት ስድስት ወራት 3.28 ቢሊዮን ዶላር አስደናቂ አፈጻጸም ማስመዝገቧን ጠቁመዋል፡፡ ኢትዮጵያ እና ጃፓን በጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የሚታወቁ በርካታ የትብብር እድሎችን የፈጠረ የረጅም ጊዜ ትብብር እንዳላቸውም ጠቅሰዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2023 ኢትዮጵያ 114 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያላቸው ሸቀጦችን ወደ ጃፓን ልካለች፡፡ በዋነኛነት ቡና 79 በመቶውን ሲይዝ ሰሊጥና አበባ ይከተላሉ፡፡ በዚሁ አመት ከጃፓን ወደ 375 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ምርት በዋናነት ተሽከርካሪዎች ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል፡፡ ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በሁለቱ ሃገራት መካከል በተለይም በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በኢነርጂ እና በቴክኖሎጂ ያለው ሰፊ የኢኮኖሚ ትስስር ዕደል ከተጠቀምን የላቀ ውጤት ማግኘት እንደምንችል አመላክተዋል፡፡



በተመሳሳይ ዕለት ክቡር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) የኢትዮጵያና የጃፓን የንግድና ኢንቨስትመንት ሲምፖዚየም ተሳታፊዎች ጋር በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ቅጥር ግቢ ቆይታ አድርገዋል፡፡ በቆይታቸውም የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ አውደ ርዕይ ማዕከልን አስጎብኝተዋቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ባላት የተለያየ መልከዓ ምድር ምቹ የአየር ንብረት ብዝሃ-ምርቶችን አምርታ ለዓለም የማቅረብ ዕምቅ አቅም እንዳላትም ለልዑካን ቡድኑ አስገንዝበዋል፡፡

“ማዕድን እንደማሳያ ብንወስድ ባለፉት ስድስት ወራት ከወርቅ ብቻ 1.36 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝተናል፡፡ አቅማችንን አጎልብተን ወደ ገቢራዊ ውጤት መቀየርና በልኩ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ እኛም ይህን ተሳቢ በማድረግ በጃፓን ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በጥራትና በብዛት ለመላክ በሚያስችል መልኩ ለልዑካን ቡድኑ ግንዛቤ ሰተናል” ብለዋል፡፡ የቡና፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ ሰብሎች፣ ቅመማቅመም፣ አትክልትና ፍርፍሬ፣ ማዕድንና ሌሎች ምርቶቻችንን በጥራት አምርተን በውጪ ንግድ የዓለም ገበያ ያለን ድርሻ እያሻሻልን ከሄድን ከዘርፉ የምናገኘው ገቢ በብዙ እጥፍ እንደሚጨም ተናግረዋል፡፡







**ጥር 15 : 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) የንግድ ስርዓት መሰረት የሚሆኑ ቁልፍ ተግባራትን ያከናወኑበት ዕለት ነው። በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የበለጸገና የሃገራችንን የግብይት ስርዓት ከመሰረቱ የሚቀይር የበየነ-መረብ (ኦንላይን) ግብይትን አስጀምረዋል።

አዲሱ የበየነ-መረብ ግብይት ስርዓት የንግዱ ዘርፍ በሃገራችን ኢኮኖሚ ተገቢውን ድርሻ እንዲወጣ የሚያስችል፣ ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጥና ለወጪ ንግዳችን ብዝሃነት ትልቅ ግብዓት የሚሆን ነው ብለዋል። የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር ከደላላ የጸዳና አምራችና ነጋዴ ከያሉበት በቀጥታ የሚገናኙበት ስርዓት ነው። ከንግዱ ማህረሰብና ከመላው ህዝባችን ጋር በመተባበር የግብይት ስርዓታችንን በማዘመን አምራቾች የአካታች የፋይንስ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑም ለምንሰራው ስራም አጋዥ ይሆናል ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ አሰራሮችን በሃገራችን በማስጀመር ፈጣንና አካታች ኢኮኖሚን ለማሳካትም ያግዛል ብለወል። ክቡር ሚኒስትሩ በዚሁ መድረክ ላይ የዲጂታል ግብይትን ጽንሰ ሀሳብ ያነገበ አዲሱን የኢትዮያ ምርት ገበያ መለያ ምልክት (ሎጎ) ይፋ አድርገዋል።

በሌላ ሁነት ደግሞ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ህንጻ ግንባታ የመሰረተ ድንጋይ ያስቀመጡ ሲሆን ይህ ባለ 24 ወለል ህንጻ በመዲናችን አዲስ አበባ ሜክሲኮ አካባቢ የሚገነባ ነው። የህንጻው ግንባታ የአጠቃላይ የለውጥ ፓኬጃችን አካል ነው ያሉት ሚኒስትሩ ሲጠናቀቅ ለቀልጣፋና አካታች ግብይት ምቹ የስራ ከባቢን የሚፈጥርና ለጀመርነው የዲጂታል ገበያ ስርዓትም ትልቅ ግብአት ነው ብለዋል።



**ጥር 16 : 2017** የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ሃገራት ዋና ኃላፊ አምባሳደር ሃሚድ አስጋር የተመራን ልዑክ ተቀብለው በሁለቱ ሃገራት የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነት ዙሪያ ውይይት አድርገዋል። ፓኪስታንና ኢትዮጵያ ዘመናትን የተሻገር ሁለንተናዊ ግንኙነት አላቸው ያሉት ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ሁለቱ ሃገራት ባላቸው የህዝብ ብዛትና የማምረት ዕምቅ አቅም በትብብር ከሰሩ የላቀ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረሳቸውን አመላክተዋል፡ ፡ በሚቀጥለው ግንቦት ወር ፓኪስታን በአዲስ አበባ ለሚታዘጋጀው ኤክስፖም ድጋፋቸውን እንደሚሰጡ ተናግረዋ። በፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ሃገራት ዋና ኃላፊ አምባሳደር ሃሚድ አስጋር በበኩላቸው ኢትዮጵያ ላሳየችው የውጭ ንግድ ዕድገት አድናቆታቸውን የሰጡ ሲሆን በቀጣይ ኢትዮጵያ ምርቶች በፓኪስታን ገበያ በስፋት እንዲቀርቡ ለማመቻቸት ቃል ገብተዋል።





**ጥር 17 : 2017** የንግድ ቀጣናዊ ትስስር ክቡር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በድሬደዋ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ተሰማርተው የንግድ ስራ ለማከናወን ማመልከቻ አስገብተው እና ተመርጠው ወደ ስራ የሚገቡ 7 ድርጅቶች የቦታ ርክክብ በሚያደርጉበት ስነ-ስርዓት ላይ ተገኝተው መልዕክት አስተላልፈዋል። ነሐሴ 2014 ዓ.ም በኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ በይፋ ተመርቆ ስራ የጀመረው የነፃ ንግድ ቀጠና በተለያዩ ተቋማት ቅንጅት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውነው የኦፕሬሽን ስራውን በማሳለጥ ላይ እንደሚገኝ ሚኒስትሩ በመድረኩ ላይ ተናረዋል። “በልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ውስጥ ቦታ ተረክባችሁ ስራ ለጀመራችሁ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት እንኳን ደስ አላችሁ” ብለዋል።



**ጥር 30 ፡ 2017** የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት በተሳታፊ ሃገራት ብዛት በዓለማችን ትልቁ አካባቢያዊ ውህደት በመሆኑ ብሄራዊ የትግበራ ስትራቴጂው የሃገራችንን ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ መሰነድ እንዳለበት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዲኤታ ወ/ሮ ያስሚን ወሀብረቢ ገልጸዋል።



ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት በተዘጋጀው ብሔራዊ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ረቂቅ የትግበራ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ከተጠሪ ተቋማት ተወካዮች ጋር ምክክር ተደርጓል። የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዲኤታ ወ/ሮ ያስሚን ወሀብረቢ በምክክር መድረኩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ለአንድ ሃገር የኢኮኖሚ እድገት ሞተር ከሆነው ንግድ ከፍ ያለ ጥቅም ማግኘት የሚቻለው አስተማማኝና ተገማች የገበያ መዳረሻ መፍጠር ሲቻል ብቻ ነው ብለዋል።

የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት በተሳታፊ ሃገራት ብዛት በዓለማችን ትልቁ አካባቢያዊ ውህደት ነው ያሉት ሚኒስትር ዲኤታ ወ/ሮ ያስሚን፣ ለሃገራችን ትልቅ የገበያ መዳረሻ እንዲሁም ለአምራች ኢንዱስትሪዎቻችን ሰፊ የጥሬ ዕቃ ምንጭም እንደሚሆን ገልጸዋል። በስትራቴጂው ዝግጅት ላይ የተሳተፉት የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተወካዮች የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ብሔራዊ የትግበራ ስትራቴጂ ሁሉንም የስምምነቱን ክፍሎች የሚዳስስና በውስጡ በበርካታ ተቋማት የሚተገበሩ ዝርዝር የድርጊት መርኃ-ግብር መያዙን ገልጸዋል።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከመፈረም ባሻገር ተግባራዊ ለማድረግ ከጫፍ የደረሰው የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት የሚፈጥረውን የገበያ ዕድል አሟጦ ለመጠቀም የትግበራ ስትራቴጂው መዘጋጀቱ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም ሚኒስትር ዲኤታ ወ/ሮ ያስሚን ተናግረዋል። ከጎረቤት ሃገሮች ባለፈ በሌሎች አፍሪካ ሃገራትም ሌሎች የገበያ አማራጮችን ከማሳየት አንጻር የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጠና ትልቅ አቅም እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

